እውነታ ጽሁፍ ወረቀት

# የማንነት ማስረጃ

## ለማንነት ማስረጃ የማረጋገጫ ሰነዶች

በቪክሮድ/VicRoads ቀጠሮ ሲያቀናጁ (ለምሳሌ፡ ተሽከርካሪን ለማስመዝገብ ወይም የመንጃ ፈቃድ ለማውጣት) የርስዎን ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርብዎታል። ትክክለኛ የሆኑ ሰነዶችን ካላቀረቡ የርስዎን ማመልከቻ ማጠናቀቅ አይችሉም። ቀጠሮ በሚያቀናጁበት ጊዜ ምን ዓይነት የማንነት መግለጫ ማስረጃ ማምጣት እንዳለብዎ ስለመጠየቅዎ ያረጋግጡ።

የውሸት እና/ወይም አደናጋሪ መረጃ ወይም ሰነዶች ማቅረብ ከባድ ወንጀል እንደሆነና ሊያስቀጣዎ ወይም እስር ቤት ሊያስገባዎት ይችላል።

## ምን ዓይነት የመታወቂያ ሰነዶች ያስፈልጉኛል?

ለማንኛውም ማመልከቻ የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርብዎታል:

- አንድ የደረጃ/category A ሰነድ (ከዚህ በታች ያለን ዝርዝር ማየት)

**እና**

- አንድ የደረጃ/category B ሰነድ (በሚቀጥለው ገጽ ያለን ዝርዝር ማየት)

ከነዚህ ሰነዶች ውስጥ ቢያንስ አንደኛው በቪክቶሪያ ነዋሪ መሆንዎን የሚያሳይ ወቅታዊ አድራሻን ማካተት አለበት። ይህን ካልሆነ ተጨማሪ ሰነዶችን ማቅረብ አለብዎ።

## ተቀባይነት ያላቸው የማንነት መታወቂያ ሰነዶች

የማንነት መታወቂያዎች የመጀመሪያው ኦርጂናል መሆን አለባቸው። ቅጂዎች ተቀባይነት የላቸውም። ከእንግሊዝኛ ባሻገር በሌላ ቋንቋ የተጻፉ ሰነዶች ከተረጋገጠ ትርጉም ጋር አብሮ መቅረብ አለበት። በውጭ አገር ቋንቋ ሰነዶችን የያዙ አመልካቾች፣ በራሳቸው ክፍያ ወደ እንግሊዝኛ ማስተርጎም አለባቸው።

የውጭ አገር ቋንቋ ሰነዶች ትርጉም መጠናቀቅ ያለበት:

- በ NAATI ተቀባይነት ያገኘ (ማንኛውም ደረጃ) ተርጓሚ፣ ወይም
- አውስትራሊያ ባለ ትክክለኛ ቆንስላ ቢሮ፣ ወይም
- የመጀመሪያ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆነ አገር ባለ የትርጉም ባለሥልጣን

## ለደረጃ/Category A ሰነዶች

- የአውስትራሊያ ፓስፖርት (ወቅታዊ የሆነ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ጊዜ የሚያበቃ)
- የውጭ አገር ፐስፖርት (እስከ ሁለት ዓመት ተቀባይነት ያለውና ከዚያም ጊዜው ያለፈበት የውጭ አገር ፓስፖርት። በቋሚነት ስለመኖር የሚገልጽ ትክክለኛ የአውስትራሊያ ሰነድ ማስረጃ፤ እንደ የቋሚ ወይም የነውአሪነት ቪዛ ማቅረብ ከቻሉ)
- የአውስትራሊያ ልደት ምስክር ወረቀት ወይም በልደት፣ በሞትና በትዳር መዝገብ ቤት በኩል የተሰጠ የስም ምዝገባ። ከልደት የተውጣጣ መረጃ እና በልደት ምስክር ወረቀት ላይ መታሰቢያ ማክበር ተቀባይነት የላቸውም።
- በፓስፖርት ጽህፈት ቤት የተሰጠ የማንነት መግለጫ ሰነድ (ብዙጊዜ ወደ ኖርትፎርድ/Norfolk ደሴት ለሚጓዙ ይሰጣል)
- የአውስትራሊያ ፖሊስ ሀይል መኮንን ፎቶ ያለበት መታወቂያ ካርድ
- በውጭ ጉዳይና ንግድ መምሪያ በኩል የተሰጠ ፎቶ ያለበት የቆንስላ መታወቂያ ካርድ
- የአውስትራሊያ ተወላጅ መሆን ወይም የዜግነት ማስረጃ ሰነድ፣ ወይም ወደ አውስትራሊያ ለመጓዝ ሰነድ ወይም በኢሚግሬሽንና ዜግነት መምሪያ ወይም በፓስፖርት ቢሮ የተሰጠ የቪዛ ማስረጃ ካርድ
- የአውስትራሊያ ፎቶ ያለበት የመንጃ ፈቃድ ወይም የተፈቀደ (ፎቶ ያለበት መንጃ ፈቃድ ማለት ወቅታዊ የሆነ ወይም ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ የሚቃጠል ማንኛውም የአውስትራሊያ ፎቶ ያለበት አሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ ወይም የለማጅ ፈቃድ ሲሆን ወይም ወቅታዊ የሆነ ወይም ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚቃጠል የቪክቶሪያ ጀልባ አንቀሳቃሽ ፈቃድ ወይም የቪክቶሪያ ጦር መሳሪያ ፈቃድ ነው)
- የኒውሳውዝ ዌልስ/NSW ፎቶ ካርድ (ከታህሳስ/December 14 ቀን 2005 ዓ.ም በኋላ በኒውሳውዝ ዌልስ/NSW RTA የተሰጠ)

**ወይም**

- በአሁኑ ጊዜ በቪክሮድስ የተያዘ ፎቶ ገጽታ

## ለደረጃ/Category B ሰነዶች

ከዚህ በታች ካሉት ሰነዶች አንዱ:

- ሜዲኬር/Medicare ካርድ
- ለጡሮተኛ የዋጋ መቀነሻ ካርድ
- ለአገለገለ ወታደር ጉዳይ መምሪያ ካርድ
- በኮመንዌልዝ የሚሰጥ ወቅታዊ የሆነ መፍቀጃ ካርድ
- የተማሪ መታወቂያ ካርድ
- ከባንክ፣ ከህንጻ ማሕበር ወይም ከብድር ማሕበር የክሬዲት ካርድ ወይም የአካውንት ካርድ
- በመስተዳድር ግዛት ወይም በፌደራል መንግሥት የተቀጣሪ ፎቶ ያለው መታወቂያ ካርድ
- የእድሜ ማስረጃ ካርድ፣ የሚስጢራዊ መክፈቻ/Keypass ካርድ
- የአውስትራሊያ መከላከያ ሀይል ፎቶ ያለው መታወቂያ ካርድ (ሲቪል የሆኑትን ሰራተኞች አያካትትም)

**ወይም**

ወቅታዊ የሆነ ወይም ከአንድ ዓመት በላይ ያልበለጠው ከሚከተሉት ሰነዶች አንዱ:

- የባንክ ቁጠባ ደብተር ወይም የባንክ አካውንት ጽሁፍ መግለጫ
- የተለፎን፣ ጋዝ ወይም የኤሌትሪክ ፍጆታ መጠየቂያ ደረሰኝ

**ወይም**

ወቅታዊ የሆነ ወይም ከሁለት ዓመት በላይ ያልበለጠው ከሚከተሉት ሰነዶች አንዱ:

- የመራጭ መመዝገቢያ ካርድ
- ከውትድርና አገልግሎት መሰናበቻ ወረቀት
- በቪክቶሪያ ደንበኛ ጉዳይ የተሰጠ የእድሜ ማረጋገጫ ካርድ
- በቪክቶሪያ ወቅታዊ የሆነ የመንዳት ስልጣን በፎቶ የተደገፈ መታወቂያ ካርድ
- የውሀ ቀረጥ ክፍያ
- የምክር ቤት ግብር
- የመሬት ዋጋ ተመን ማሳሰቢያ

## የቪክቶሪያ ነዋሪ ስለመሆን ማስረጃ

በቪክቶሪያ የሚኖሩበት አድራሻ **ካልተገለጸ** ወይም በደረጃ/ category A ወይም B ማስረጃ ሰነዶች ላይ ካለው **የተለየ** ከሆነ ከዚህ የሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ **አንደኛው** ያስፈልግዎታል።

- አሁን ባሉበት አድራሻ የሚያሳይ የሽያጭ፣ የውል ስምምነት ኩንትራት ወይም የኪራይ መጠን ሰነድ።
- የመንጃ ፈቃድ ወይም የተሽከርካሪ ምዝገባን በአሁን ጊዜ ለማሳደስ ማሳሰቢያ
- በአውስትራሊያ ግብር ቢሮ የተደረገ ግምገማ (ባለፈው ወይም በአሁኑ የፋይናንሻል ዓመት)

በቪክቶሪያ ነዋሪ ስለመሆንዎ አሁንም ማስረጃ ማቅረብ ካልቻሉ፣ ተያዥ ከሚሆን ሰው ጽሁፋዊ መግለጫ እንደሚከተለው ማቅረብ አለብዎ:

- እርስዎን ለ12 ወራት ወይም ከዚያ በላይ በሚያውቅዎና የቪክቶሪያ መንጃ ፈቃድ ባለው መፈረም አለበት፣ እንዲሁም
- የርስዎን ስምና አድራሻ ማካተት እንዳለበትና
- የተያዥው ስም፣ የመንጃ ፈቃድ ቁጥርና ፊርማ መኖር አለበት።

ይህ ጽሁፋዊ መግለጫ በመንጃ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ላይ እንደተሰጠና ይህም ከማመልከቻ ሂደቱ እንደ አንዱ አካል ሆኖ መሞላት አለበት።

## ስምን የመቀየር ማስረጃ

በደረጃ/ category A ወይም B ማስረጃ ሰነዶች ላይ ካለው **የተለየ** ከሆነ ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ **አንደኛው** ያስፈልግዎታል:

- በአውስትራሊያ ውስጥ በልደት፣ ሞትና ጋብቻ መመዝገቢያ ቢሮ የተሰጠ የጋብቻ ምስክር ወረቀት
- የፍች ወረቀቶች (ስሙ ወደ ቀድሞ መመለሱን የሚያሳይ)
- በድምጽ ጀብዱ ግኝት (በቪክቶሪያ ውስጥ ከህዳር/November 1986 ዓ.ም በፊት የተሰጠ)
- የምስክር ወረቀት ስም ቅያሬ (በቪክቶሪያ ውስጥ ከህዳር/November 1986 ዓ.ም በኋላ የተሰጠ)

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ vicroads.vic.gov.au ላይ መጎብኘት ወይም በስልክ 13 11 71 መደወል ወይም ወደ ቪክሮድ/VicRoads የደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል መሄድ ነው።

*በዚህ እውነታ ጽሁፍ ወረቀት ውስጥ የቀረበው መረጃ በሚታተምበት ጊዜ ትክክል እንደሆነና ከዚያም ሊቀየር ይችላል።*

VRPIN02900 Evidence of Identity – Amharic Authorised by VicRoads, 60 Denmark Street, Kew, 3101